# በኢትዮጵያ የብሔረሰቦችን ጥያቄ በተመለከተ

በዋለልኝ መኮንን ህዳር 8፤ 1962 ዓ.ም. ተጻፈ

(Arts IV, HSIU; Nov. 17, 1969)

ትርጉም፡- ወንድይራድ አስማማው

© May 31, 2018

የዚህ ጽሁፍ ዐብይ አላማ በዚህ ሃገር አይነኬ ነገር ግን ወሳኝ ጉዳይ በሆነው የብሔረሰቦች ጥያቄ በተመለከተ ውይይት መጫር ነው። ጽሁፉ ለልዩ ክበረ በዓል የተዘጋጀ በመሆኑ በጥቅል ብያኔ የተሞላ ነው። በጊዜ እጥረትና ሌሎች እክሎች ምክንያት ጥልቅ ትንታኔ መስጠት የሚቻል አልሆነም። ለመነሻ ያህል ግን እርባነ የለሽ አይደለም ብዬ አምናለሁ። አንባቢያን ሀረጋትን ከአውዳቸው ውጭ እየነጠሉ ከማጋነን አዝማሚያ እንደሚቆጠቡ ተስፋ አደርጋለሁ። ይልቁን እዚህ ላይ የተነሱ ነጥቦች ከቀረበው ጥቅል ትንታኔ አኳያ ሊታዩ ይገባል።

በተማሪዎች ንቅናቄ ሂደት ውስጥ አሁን አዲስ ምዕራፍ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሶሻሊዝም ሳይታለም የተፈታ የተማሪዎች ርዕዮተ ዓለም ከዚህ ውጭ የሆነው አድሃሪነት ከነግሣንግሥ ማማለያው ተሸናፊ የሆነበት ነው፡፡ ከእንግዲህ የቀረው ፍትጊያ፤ አብዮት ወይስ ጥጋናዊ ለውጥ በሚሉ ተጻራሪ ኃይሎች ሳይሆን፤ በትክክለኛው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መመራት ወይስ የተበረዘ በሚሉት መካከል ነው፡፡

በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ያሉ የሶሻሊዝም ኃይሎች ባላቸው ሰዎች በተሣሣተ መንገድ ሊረዱን ይችላሉ የሚል ስጋት፣ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በግልፅ ለመወያየትና አደገኛና የማይመች አድርገው ያዩታል፡፡ ስሱ ከሆኑት ከነዚህ ጉዳዮች አንዱ የብሔረሰቦች ጥያቄ ነው። በርግጥ አንዳንዶች አግባብ ባልሆኑ መንገድ ጎሰኝነት ሲሉ ይጠሩታል እኔ ግን ብሔርተኝነት ብዬ መጥራትን እመርጣለሁ፡፡ የፓናል ውይይቶች፣ በታገል መፅሔት የሚወጡ ጽሁፎችና የመድረክ ተናገሪዎች የህቡዕ በራሪ ወረቀቶች እንዲሁም የጥናት ክበቦች ሳይቀር ለዚህ ጉዳይ ትኩረት አልሰጡትም፡፡ በርግጥ የዚህ ጉዳይ መነሳት የተወሰነውን የተማሪ ማህበረሰብ እንዳይነጥል፤ መንግስትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ ይህን ቅን ውይይት፤ አብዮተኛ የሆነውን የተማሪዎችን ንቅናቄ ዋጋ ለማሳጣት [ጥላሼት ለመቀባት] ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

ከአምና ጀምሮ ጥቂት የሆኑ ስብስቦች ይህንን ስስ ጉዳይ ለብቻቸው በመሆን ሲወያዩበት ቆይተዋል፡፡ ውይይቶቹም በግልፅ ስላልተደረጉ፤ በግል ደረጃ የተደረጉ ውይይቶች ሳይቀሩ እያፈተለኩ

በመውጣታቸው፤ ለሀሜት፣ አለመግባባቶች እና ለተጋነነ አሉቧልታ ዳርጓል። እንደ እኔ፣ ተማሪዎች ማንኛውም ዓይነት ዕውነታ፣ እጅግ ስሜት የሚነካም ቢሆን ለመጋፈጥ ብቁ ናቸው ብዬ አምናለሁ። በመሆኑም ላለፉት ሁለት ሳምንታት በተሠራጩት) የተዛነፈ ሃሳብ ያዘሉ በራሪ ወረቀቶችና ለሚታዬው መዝቀጥ መፍትሄው ግልፅ ውይይት ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ስንል እነ ማንን ነው? እዚህ ላይ ህዝቦች ያልኩት ሆን ብዬ ነው፤ ምክንያቱ በማህበረሰብ አጥኚዎች (Sociologists) አተያይ፣ አሁን ባለችበት ደረጃ ኢትዮጵያ አንድ ብሔር አይደለችም። ይልቁንስ ኢትዮጵያ የራሳቸው ቋንቋ፣ የአለባበስ ስርዓት፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ አደረጃጀት እና ግዛታዊ ማንነት ያላቸው ደርዘን ብሔረሰቦች ውጤት ናት። ብሔር ስንልስ ምን ማለት ነው? የራሱ ሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የራሱ የሆነ አለባበስ ሥርዓት፣ የራሱ የሆነ ታሪክ፣ የራሱ የሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀት አይደለም? ስለዚህ በኢትዮጵያ የኦሮሞ ብሔር፣ የትግራይ ብሔር፣ የአማራ ብሔር፣ የጉራጌ ብሔር፣ የሲዳማ ብሔር፣ የወላሞ (የወላይታ) ብሔር፣ የአደሬ (ሀረሬ) ብሔር፣ እና የፈለገውንም ያህል ባይመቻችሁም÷ የሶማሌ ብሔር አለ ብዬ መደምደም አልችልምን? እውነተኛው የኢትዮጵያ ገፅታ ይህ ነው። በርግጥ በገዥ መደቦች የተፈጠረው እና ሳይፈልጉ የተጫነባቸው እንዲሁም አልፎ ተርፎ ምንም በማያውቁ ተጓዦች ብዙ የተባለለት ሃሳዊ የሆነው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አለ።

ይሄ ውሸት የሆነው ብሔርተኝነት ምንድን ነው? በቀላሉ የአማራ፣ አንዳንዴ የአማራና ትግሬ የበላይነት አይደለምን? እስኪ ማንንም ሰው የኢትዮጵያ ባህልን ጠይቁት፣ እስኪ ማንንም «የኢትዮጵያ ቋንቋ ምንድን ነው?» በሉት፣ እስኪ «የኢትዮጵያ ሙዚቃ የቱ ነው?» በሉት፣ «የትኛው ነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አልባስ ብላችሁ» ጠይቁት። የአማራ ወይም የአማራና ትግሬ ነው!!

አንድ ሰው «እውነተኛ ኢትዮጵያዊ» ለመሆን፤ አማርኛ መናገር፣ አማርኛ ሙዚቃ ማዳመጥ፣ የአማራና ትግሬ ሃይማኖት የሆነውን ኦርቶዶክስ ክርስትና መቀበል፣ እና የአማራና ትግሬ የሆነውን ሸማ በዓለማዓቀፍ ጉባኤዎች መልበስ አለበት። አንዳንዴ «ኢትዮጵያዊ» ለመሆን ስማችሁን ሁሉ መቀየር ይኖርባችሁ ይሆናል። በአጭሩ ለመጠቀም ኢትዮጵያዊ ለመሆን (የፋኖንን አገላለፅ ልጠቀምና) የአማራነት ጭምብል ማጥለቅ አለብህ። የብሔር ማንነታችሁን ማንፀባረቅ ስትጀምሩ ወዲያውኑ ጎሰኛ ተብላችሁ ትፈረጃላችሁ። ይሄም የሚሆነው አማራ ሁኖ ለመወለድ ካልታደላችሁ ነው። በህገ መንግስቱ መሠረት ትምህርት ቤት ለመግባት፣ ሥራ ለማግኘት፣ መጽሐፍት ለማንበብ (ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆንም)፣ ዜና እንኳን ለማዳመጥ ሶማሌ ወይም አስመራ የሚኖር ኤርትራዊ ካልሆንክ በስተቀር አማርኛ ማወቅ ግድ ይልሃል።

ስለ ማርክሲዝም በስሱም ቢሆን ላወቀ ሰው፣ ባህል ማለት ለምጣኔ ሃብት መሠረት የሆነ ግንባታ ከመሆን ያለፈ ነገር አይደለም። በመሆኑም ሁሌም የባህል የበላይነት ኢኮኖሚያዊ የበላይነትን ይቀድማል። ለዚህ ጥሩ ማሣያ ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ያለው የአማራ፤ በተወሠነ መልኩ ደግሞ የትግራይ ነፍጠኛ ሥርዓት ነው። በከተሞች የሚታዩ የአማራና ትግሬ ቅንጅት ነው። የተለመደው÷ ይህን ሃሳብ ለማጣጣል የሚቀርበው ሃሳዊ ሃሳብ ደግሞ በገጠር ውስጥ በድህነት የሚማቅቀውን ሠፊ የአማራና ትግራይ ህዝብን ማጣቀሻ አድርጎ መከራከሪያ አድርጎ ማቅረብ ነው። በነገራችን ላይ በብሪታኒያ ኢምፔሪያሊዝም ወቅትም ቢሆን ሰፊው የብሪታኒያ ሠራተኞች ኢሰብዐዊ በሆነ አኳኋን ውስጥ ይኖሩ ነበር።

ሌላው የሞቀ መከራከሪያ ሃሳብ በካቢኔት ውስጥ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ አማራና ትግሬ ያልሆኑ ሚኒስትሮችን መጥቀስ ነው፣ አንድ ወይም ሁለት ጀኔራሎችን ከሰራዊቱ መጥቀስ፣ አንድ ወይም ሁለት አስተዳዳሪዎችን እና ገጠር ያሉ ደርዘን ባላባቶችን መጥቀስ ነው። ነገር ግን ለምሣሌ እንደ ብሪታኒያ ዓይነት ኢምፔሪያሊስቶች ከዚህ በበለጠ (በያንዳንዱ ጉዳይ) ቅኝ ግዛቶቻቸውን ለመግዛት ከአንድ ብሪታኒያዊ የበለጠ ሃብታም በሆኑ የጎሳ መሪዎች ይደገፉ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ (ሁፌት) ቦይኝ (Houphet Boigne) እና ሴንጎር እኮ የፈረንሳይ ብሔራዊ ሸንጎ አባላት የነበሩ ሲሆን፣ አልፎ ተርፎም ሚኒስትር ነበሩ ሆኖም ቅንጣት ታክል የፖለቲካ ነጻነት ለሴኔጋላዊያንም ሆነ አይቮሪኮስታዊያን አላጎናጸፋቸውም።

በርግጥ በአማራዎችና ተከታይ አጋራቸው በሆኑት ትግሬዎች የተደረገው የኢኮኖሚና የባህል ወረራ የታሪከ አጋጣሚ ብቻ ነው። አማራዎች የበላይ የሆኑት፣ በተፈጥሮ ኢምፔሪያሊስትነት የተጠናወታቸው ስለሆኑ አይደለም ። ዕድሉን ቢያገኙ ኦሮሞዎች ሊያደርጉት ይችሉ ነበር፤ ወላሞዎቹ (ወላይታዎች) ሊያደርጉት ይችሉ ነበር፤ ታሪክም ይህን ሊያደርጉ እንደነበር ይመሠክራል። ነገር ግን ለዚህ ሁኔታ መቀጠል ምክንያት ሊሆን አይገባም። አጣዳፊው ጉዳይ «በቃ!» ብለን ማወጅ አለብን ነው። እናም እውነተኛው ብሔራዊ-ሃገር (National State) መገንባት አለብን።

ብሔራዊ-ሃገር ስንል ምን ማልት ነው? ብሔራዊ-ሃገር ስንል ሁሉም ብሔረሰቦች በአገር ጉዳይ ላይ በእኩልነት የሚሳተፉበት፤ እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱን ቋንቋ፣ ሙዚቃ እና ታሪክ ለመጠበቅና ለማሣደግ እኩል ዕድል የሚያገኝበት ሃገር ማለት ነው። አማራዎች፣ ትግሬዎች፣ ኦሮሞዎች፣ አደሬዎች (ሀረሪዎች)፣ ሶማሊዎች፣ ወላሞዎች (ወላይታዎች)፣ ጉራጌዎች፣ ወዘተ በእኩል የሚስተናገዱበት ሃገር ማለት ነው። በኢኮኖሚም ሆነ በባህል አንደኛው ብሔር ሌላውን ብሔር የማይጫንበት ሃገር ማለት ነው። ታዲያ እንዴት ነው ይህን እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ርትዐዊ ሃገር መፍጠር የሚቻለው?

በወታደራዊ ሃይል ይህን ማድረግ ይቻላል? በፍፁም!! ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ማለት ከግለሰቦች ለውጥ ያለፈ አይደለም። ምናልባትም ካለው ሥርዓት የተሻለ ነጻነት ይኖረው ይሆናል። ነገር ግን በመደቦች መካከልም ሆነ በብሔረሰቦች መካከል ያለውን ተቃርኖ መፍታት አይችልም። የመንግስቱና[1] ታደሰን መፈንቅለ መንግስት ሙከራን ብናነሳ፣ የታየው ምላሽ ማንም የሚረሳው አይመስለኝም። የመንግስቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ (ምንም እንኳ የቤተሰብ እና በዋነኝነት የሸዋ አማራዎች (በርግጥ የተወሰኑ ልዩ የሆኑ ነበሩ ልክ እንደ ወርቀነህ ገበየሁ[2] ዓይነቶች) ከፍተኛ ተቀባይነት ነበረው ምክንያቱም "በኢትዮጵያዊያን" - ማለትም በአማሮች - የተሞከረ ነዋ። የታደሠ[3] ሲሆን ግን ወዲያውኑ የጎሰኞች አመጽ ተደረገ። ለምን? ኦሮሞ የሆነው ታደሰ ለኦሮሞ የበላይነት እንጅ መፈንቅለ መንግስት ማካሄድ አይችልም ማለት መሆኑ ነው።

መፈንቅለ መንግስትን ከማውገዝ ወደ ኋላ አልልም። ነገር ግን የታደሠ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ አንድ ወሳኝ ጠቀሜታ ነበረው። ኦሮሞ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለራሳቸው ክብር እንዲሠጡ አድርጓል። ለራስ ክብር መሥጠት ደግሞ ህዝብን መሠረት ያደረገ አብዮት ለማካሄድ ቅድመ ሁኔታ ነው። መፈንቅለ መንግስቱን ሲያናንቁ የነበሩት አብዮተኛ ነን ባይ ተማሪዎች እንኳ ይህን ጠቃሚ ጎን መረዳት አልቻሉም። የአማራ-ትግሬ የበላይነት ስሜት ምንነትን በዚህ እንኳ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ጉዳይ የመንግስት ፕሮፓጋንዳ ውጤቶች ከመሆን ባለፈ ምንም አለመሆናቸውን አርጋግጠዋል።

የኤርትራ ነጻነት ግንባርና የባሌ ትጥቅ ትግል ግባችንን ያሳኩልናል? ግባችንን የሚያሳኩልን አሁን ባሉበት ዓላማም ሆነ አኳኋን አይደለም።

እነዚህ ሁለቱም ንቅናቄዎች በጠባያቸው የተለያዩ ናቸው። የኤርትራ ነጻነት ግንባር በአካባቢው ከበርቴ ባለሃብት (bourgeoisie) የሚመራ ሲሆን፣ የባሌ ትጥቅ ትግል ደግሞ በአካባቢው ፊውዳሎች የሚመራ ነው። ለእኛ ግብ የሚበጀውን ዓለማቀፋዊ ዕይታ አልያዙም። ብሔራዊ ጭቆና መኖሩን ማወጃቸው ያለምንም እንከን ትክክል ናቸው። በዚህ ላይ የሚያጋጨን ጉዳይ የለም። ነገር ግን የእነሱ አስተሳሰብ እዛው ላይ ለማቆም ነው። ባለው አገዛዝ መሠረት ላይ ሠፊ መሠረት ያለው ጥቃት ለመፈፀም አልሞከሩም። በአጭሩ እኒህ ንቅናቄዎች በአርሶ አደሮችም ሆነ በሠራተኞች የተመሩ አይሉም። ለሰፊው ህዝብ፤ የጌታ ለውጥ ከመሆን ያለፈ አይሆንም ነበር። ለሶሻሊስቶች የሠፊው ህዝብ ተጠቃሚነት ከሁሉም ነገር ቀዳሚ ጉዳይ ነው።

---

[1] የ1953 መፈንቅለ መንግስት ጠንሳሽ የነበረውን ብርጌደር ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ ለማለት ነው።
[2] ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የጎንደር ጠቅላይ ግዛት ተወላጅ ነበሩ።
[3] ብርጌደር ጀኔራል ታደሰ ብሩ

ስለጎጃም አመጽም ተመሳሳይ ማለት ይቻላል። አሁንም በዚህ አጋጣሚ በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ምን ያህል የአማራ የበላይነት ቅቡል እንደሆነ ላሳይ።

የኤርትራ ነጻነት ግንባርን መደገፍ ሃጢዓት ነው። አንዳቾ እንኳ ጥሩ ነገር ስለ ኤርትራ ነጻነት ግንባር ከተጻፈ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሕብረት (USUAA – University Students Union of Addis Ababa) ሆነ በኢትዮጲያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብሔራዊ ሕብረት (NUEUS - National Union of Ethiopian University Students) ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል። ነገር ግን የጎጃም ጉዳይ ሲሆን የተለዬ ይሆናል። ይህ የእኒህን አብዮተኛ ነን ባዮች ማንነት በተጨባጭ ያሣያል።

ልብ በሉ እያልኩ ያለሁት እኒህ ንቅናቄዎች በሙሉ እውነተኛ ብሔርተኛ ሶሻሊስታዊ አገር የመመስረት ግባችንን ዕውን ለማድረግ የሚሆኑ የመጨረሻ መፍትሄዎቻችን አይደሉም። በእኔ በኩል ያለውን አገዛዝ እስከተገዳደሩት፣ እስካዳከሙት ድረስና በኋላ በእውነተኛ ሶሻሊስታዊ አብዮት ቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችል የተቃውሞ አካባቢዎችን እስከፈጠረ ድረስ እደግፈዋለሁ።

አሁንም አንድ ነገር ደግሜ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። እነዚህን ንቅናቄዎች የምቃወመው ተገንጣይ ስለሆኑ አይደለም። ተገንጣይነት ያን ያህል ችግር ያለው ጉዳይ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ብሔራዊ ጭቆና ከሚያካሂድ መንግስት ይልቅ፤ መገንጠል በጣም ይሻላል። ሌኒን እንዳለው "ሰዎች መገንጠልን አማራጭ አድርገው የሚወስዱት፤ ብሔራዊ ጭቆናና ብሔራዊ ቅራኔዎች አብሮ መኖርን መራር ሲያደርጉና ኢኮኖሚያዊ ተራክቦ እንዳይኖር ሲያደርጉ ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የመደብ ትግሉ ነጻነት የበለጠ በመገንጠል ዕውን ይሆናል። አሁንም የጥቅምቱን አብዮት የመሩት፣ ቦልሼቪኮች የተገኙበት፣ የደገፉትና የተቀበሉትን የ1986ቱ የለንደን ዓለም ዓቀፍ ሶሻሊስት ጉባኤ፣ የብሔረሰቦች ጥያቄን አስመልክቶ ያሰተላለፈውን አቋም መግለጫ ልጠቅስ እወዳለሁ። «ይህ ጉባኤ ሁሉም ብሔሮች ራሰን በራስ የማስተዳደር ሙሉ መብት የሚደግፍ ሲሆን፣ በያንዳንዱ ሃገር በወታደራዊ፣ ብሔራዊ ወይም ሌላ ዓይነት ፍፁማዊ ጨቋኝ ቀንበር ሥር ላሉ ሠራተኞችና አርሶ አደሮች ያለውን አጋርነት ይገልጻል።»

የመገንጠል ንቅናቄዎች በአርሶ አደሮችና በሠራተኞች መደብ እስከተመራና ያለባቸውን ዓለማ ዓቀፋዊነት ግዴታ እስከ ተቀበሉ ድረስ፤ ድጋፍ መስጠት ብቻ ሳይሆን ወታደራዊ ዕርዳታም ሊደረግላቸው ይገባል። አንድን ህዝብ እስክታውቅብኝ ድርስ እየበዘበዝኩህ አብረን እንኑር ማለት ፍፁም ኋላ ቀርነትና ራስ ወዳድነት ነው። በመገንጠል ጉዳይ ብዙ ጊዜ ልናጠፋ አይገባም። ይሁን እንጅ ዋናው ጉዳይ [መገንጠሉ] ተራማጅ ነው ወይስ አድሃሪ ነው የሚለው ነው። ሶሻሊስታዊ ኤርትራና ባሌ በሃገሪቱ ለሚደረግ አብዮት

ከፍተኛ ጉልበት መሆን እና ለመልሶ ውህደት የሚረዳ የእኩልነትና ዲሞክራሲያዊ መሠረት ሊጥሉ ይችላሉ።

ወደ ፍሬ ጉዳያችን ስንመለስ፣ እንዴት ነው ሃቀኛ እኩላዊ ብሔራዊ-አገር (egalitarian national state) መመሥረት የምንችለው? መልሱ ግልፅ ነው። ይህን ዓላማ ዕውን ማድረግ የምንችለው በአመፅና በኃይል ብቻ ነው፤ ማለትም በአብዮታዊ የትጥቅ ትግል ብቻ ነው። ነገር ግን ከአገዛዙ ሃሳዊ-ብሔርተኛ ፕሮፓጋንዳ ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል። አብዮቱ የትም ሊጀመር ይችላል። በተራማጅ ኃይሎች ማለትም በአርሶ አደሮችና በሠራተኛው እስከተመራ ድረስ፣ የሁሉንም ብሔረሰቦች ምጣኔ ሃብታዊና ባህላዊ ነጻነት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሠፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት እስካቀዳጀ ድረስ፤ አብዮቱ በመገንጠል ጥያቄ ሊጀምር ይችላል። የእያንዳንዱ አብዮተኛ ሃላፊነት አንድን ንቅናቄ መመዘን ያለበት፣ ተገንጣይ ነው ወይስ አይደለም በሚል ሳይሆን፤ ንቅናቄው ሶሻሊስታዊ ነው ወይስ አድሃሪ ነው በሚል ነው። አንድ ሶሻሊስታዊ ንቅናቄ ተገንጣይ ሁኖ ብቻ አይቀርም፤ ምክንያቱም የሶሻሊዝም የመጨረሻ ግብ በራሱ ዓለም ዓቀፋዊነት ነው።

በድጋሚ ሌኒን እንዲህ ይላል «ሠፊው ህዝብ በዕለ ተለት ኑሮው የመልካምድራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ትሥሥርን ዋጋ፣ የትልቅ ገበያና ትልቅ አገር ፋይዳ በደንብ ጠንቅቆ ያውቃል።» ትግሉን ከዚህ አኳያ ስንመለከተው፤ በየአቅጣጫው አጣብቂኝ ውስጥ እየገባ ያለው የእኛ ዓይነት አገዛዝ በአንጻራዊ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይገረሰስ ዘንድ ግድ ይለዋል። በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ያለው ንቃተ ህሊና የተለያዬ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ፣ ከፍተኛ የንቃተ ህሊና ደረጃ የደረሰ ብሔረሰብ፣ መጀመሪያ ራሱን ነጻ ማውጣትና በመቀጠል ሌሎች ላልተሸራረፈ ነጻነት የሚያደርጉትን ትግል የመደገፍ መብት ብቻ ሣይሆን ግዴታም ጭምር ነው ያለብን። ይህ በኮሪያ ያለ እውነታ አይደለምን? ይህን እንቅስቃሴ እንደግፋልን፤ እንደግፍም እንዴ? ታዲያ ጎሠኝነት፣ ተገንጣይነት ወዘተ የሚል ወሬ ምን አመጣው?